የሰበር መ/ቁ/211725

ሚያዝያ 28 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ ብርሃኑ አመነው

ተሾመ ሽፈራው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ ኤጀርሳ ባኬ ዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ የሾፌሮች ሰራተኞች ማህበር የቀረበ የለም

ተጠሪ፡በከልቻ በሪ የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ኃ/የተ/የግ/ማህበር-ተወካይ አቢቹ አዱኛ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ለዚህ ሰበር አቤቱታ የቀረበዉ የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤቶች ዉሳኔ በማሻሻል የሰጠዉ ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል ነዉ፡፡ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ የስራ ግንኙነት የሚመለከት ነዉ፡፡የጉዳዩ አመጣጥ ሲታይ ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሸዋ ዞን አደዓ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን ጉዳዩ የሰራተኛ ጥቅማ ጥቅም ክፍያ ጥያቄ የሚመለከት ነዉ፡፡የአሁኑ አመልካች ከሳሽ በመሆን በአሁኑ ተጠሪ ላይ በቀን 17/06/2013 ዓ.ም አሻሽሎ ባቀረበው ክስ ግንቦት 12 ቀን 2010 ዓ.ም በተፃፈው ስምምነት 228 ሰዎችን በሹፍርና የስራ መደብ ላይ ቀጥሮ እየሰራን ያለአንዳች ጥፋት ከደመወዝ ላይ በአጠቃላይ ብር 175,079.29 የቆርጠውን እንዲከፍለን፤ የ72 ሰዎች ውሎ አበል ብር 153,187.00 እንዲከፍል፤የአመት እረፍት በውላችን መሰረት ለአንድ ሰው በዓመት 30 ቀን የሚሰጥ ሲሆን ተጠሪ ግን የሹፌሮች ስራ ፀባይ እረፍት አያሰጥም በማለት የ2011 ዓ.ም ብቻ ወደ ገንዘብ ቀይሮ ከፍሎ ከግንቦት 2011 ዓ.ም እስከ ህዳር 2013 ዓ.ም ያለው የአንድ ሰው 45 ቀናት በቀን ደመወዝ ተባዝቶ 162.60*45 ብር 8667 ሲሆን በአጠቃላይ ብር 1,976,076.00 እንዲከፈለን፤ የተጨማሪ የስራ ቀናት እና የትርፍ ሰዓት ስራዎች የ1560 ሰዓት በአጠቃላይ ብር 751,140.00 ሆኖ በአጠቃላይ ተጠሪ ብር 3,230,561.58 እንዲከፍለን እንዲወሰንልን በማለት ዳኝነት

የጠየቀ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ ባቀረበው መልስ ሰራተኞች ሲሚንቶውን እንዲያደርሱ በታዘዙበት ቦታ ሳያደርሱ ባልታዘዙበት ቦታ ስላራገፉ ይህ ደግሞ ተጣርቶ የነዳጅ ዋጋና የወሰዱት አበል ከደመወዛቸው ተቆርጦ ገቢ ሆኗል፣ይሄንንም ሚያዝያ 05 ቀን 2012 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቀን ከደመወዛቸው እንዲቆረጥ ተደርጓል፣ሰራተኞቹ ሁሉ የማህበሩ አባላት መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ የለም፣የዓመት እረፍት የሚሰጠው ዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ እንጂ ተጠሪን አይመለከትም፣እረፍት የሚሰጠው ሰራተኛ ሲጠይቅ እንጂ አሰሪ እራሱ ውጣ ሊል አይችልም፣ ሰራተኞች እረፍት ጠይቀው ያጡት ነገር የለም፣አሁንም ጠይቀው መውሰድ ይችላሉ፣አበል፣የእረፍት ቀን እና ትርፍ ሰዓት ስለመስራታቸው ያቀረቡት ማስረጃ የለም፣ የተጠሪ ድርሻ ሰራተኞችን መቅጠር፣ማስተዳደር፣ማሰማራት እና ደመወዝ መክፈል እና ባደረሱት ጥፋት ኃላፊነት መውሰድ እንጂ የአመት እረፍት የሚሰጠው ተጠሪ አይደለም በሚል ዳንጎቴ ሲሚንቶ ፋብሪካ ወደ ክርክሩ እንዲገባ በማለት መከራከሩን መዝገቡ ያሣያል፡፡

ክርክሩን በመጀመሪያ የዳኝነት ስልጣን የተመለከተዉ የአዳአ በርጋ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኝ ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ያለአንዳች ማስጠንቀቂያ ደመወዛቸውን መቀነስ ወይም መቁረጥ ትክክል አለመሆኑን፤አበል የመክፈል ግዴታ የለብንም የሚለዉ ክርክር ተቀባይነት እንደሌለው፤ የአመት እረፍት በተመለከተ አሰሪ የአመት እረፍት አመቻችቶ አስፈላጊውን ቅጽ በማስሞላት ማስወጣት እንዳለበት ይህንን እስካልፈጸመ ክፍያ መፈጸም እንዳለበት፤የእረፍት ቀናት እና የትርፍ ሰዓት በተመለከተ በበዓል ቀናት እና የትርፍ ሰዓት እንዲሰሩ በግልፅ የተሰጠ ትእዛዝ እስከሌለ ድረስ ክፍያ የሚከፈልበት ምክንያት የለም በማለት በአጠቃላይ ደመወዝ ያለአግባብ የተቀነሰባቸው የ228 ሰራተኞች፣ለ72 ሰራተኞች ሳይከፈል የቀረው አበል እና የአመት እረፍት በአጠቃላይ ብር 2,304,342.29 እና 10% የጠበቃ አበል ጋር ተጠሪ ለሰራተኞች እንዲከፍል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት ግራ ቀኝ አከራክሮ ጉዳዩን መርምሮ የተቆረጠባቸው ደመወዝ፣ያልተጠቀሙበት የኣመት አረፍት እና የጠበቃ አበል ጨምሮ ብር 1,317,413.64 እንዲከፍል የተሰጠዉን ዉሳኔ ክፍል በማጽናት የ5 ወራት የአመት እረፍት በአሁኑ ጊዜ ወደ ገንዘብ ተቀይሮ መከፈል አለበት የሚባልበት ምክንያት የለም፣የውሎ አበል በተመለከተ የቀን ውሎ አበል መጠን ስንት እንደሆነና ከመቼ ጀምሮ

እንደተቋረጠ የሚሉትን  የስር ፍ/ቤት ማስረጃ አጣርቶ ፍትሃዊ ውሳኔ እንዲሰጥበት በማለት በፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ.343(1) መሰረት ወደስር ፍ/ቤት መልሶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ችሎቱም ጉዳዩ ያስቀርባል በማለት መዝገቡን መርምሮ የተቆረጠ ደመወዝ፤ውሎ አበል ክፍያ እና የጠበቃ አበል አስመልክቶ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሰኔ በማጽናት የአመት እረፍት በተመለከተ አመልካች ስራ ላይ ላሉት ሰራተኞች የአመት እረፍት ክፍያ በገንዘብ ተክቶ እንዲከፈላቸው የተሰጠዉ ውሰኔ በተመለከተ የስራ ዉል ሳይቋረጥ ወደ ገንዘብ ተለዉጦ ሊከፈል አይገባም በማለት ሽሯል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ላይ ነዉ፡፡የአመልካች አቤቱታ ይዘት፡- የዓመት እረፍት በተመለከተ በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር የ2010 ዓ.ም የውል ዘመን ተጠናቆ በሌላ አዲስ ውል ተተክቶ እያለ እና ተጠሪ ጊዜውን ጠብቆ በየተራ እረፍት ስላልሰጠንና የሾፌሮች ስራ በባህሪው የዓመት እረፍት የሚያሰጥ አይደለም፣የዓመት እረፍት የመስጠት ግዴታ የለብኝም፣ አመልካቾች አሁንም ከፈለጉ ወደ ገንዘብ ቀይረው መውሰድ ይችላሉ በማለት ጉዳዩን በማመን የተከራከረ መሆኑን፤የስር ፍ/ቤት ተጠሪ የዓመት እረፍት ለሰራተኞች ህጉን ተከትሎ ያልሰጣቸው መሆኑን አረጋግጦ ወደ ገንዘብ ለውጦ እንዲከፈለን የወሰነውን የክልል ሰበር ሰሚ ችሎች የአመት እረፍት ሊከፈላቸው አይገባም በማለት የስር ፍ/ቤት ውሳኔ መሻሩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ውሳኔው ተሽሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ እንዲፀና በማለት አመልክተዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤት የወሰናቸውን ውሳኔዎች የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጭብጦችን በመቀየር በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ያላነሳቸውን ክርክር በማንሳት መወሰኑን አግባብነት ለማጣራት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት ታዟል፡፡

ተጠሪ ባቀረበው መልስ የአመት እረፍት ወደ ገንዘብ ተለውጦ የሚሰጠው የስራ ውሉ የተቋረጠ ሠራተኛ ያልወሰደው የዓመት እረፍት ካለ ወይም በአመት እረፍት ላይ እያለ የተጠራ ከሆነ ያልተጠቀበት እረፍት ታስቦ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንደሚከፈል መሆኑን፤ ከእነዚህ ሁኔታዎች ውጪ አመልካቾች በስራ ላይ እያሉ እንዲሁም የሚሰጠው የዓመት እረፍት 16 ቀን ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት ከህግ ውጭ ወደ ገንዘብ ተለውጦ እንዲከፈል የሰጠውን ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በማረም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ

ስህተት የለዉም በማለት ተከርክሯል፡፡አመልካች አቤቱታውን በማጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የግራቀኙ ክርክር አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተመለከትነው ሲሆን ጉዳዩ ለሰበር ያስቀርባል የተባለበትን ጭብጥ መሰረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡እንደመረመርነዉ ለሰራተኞች እንዲከፈል አመልካች ከጠየቀዉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ዉስጥ አብዛኛዉ በስር ፍርድ ቤት የተወሰነለት ሲሆን በዚህ ዉሳኔ እስከ ክልሉ ሰበር ችሎት አቤቱታ ያቀረበዉ ተጠሪ ነዉ፡፡በተጠሪ አቤቱታ መነሻ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የስር ፍርድ ቤት ዉሳኔ ያሻሻለዉ የዓመት እረፍት በገንዘብ ተለዉጦ ይከፈል መባሉ አግባብ አይደለም የሚለዉ ነዉ፡፡የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ዉሳኔ ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለሰበር ችሎቱ ከተሰጠዉ ስልጣን ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

እንደሚታወቀዉ የሰበር ስርዓት በህግ አተገባበር ወይም አተረጓጎም ረገድ የተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት በማረም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር ማስቻል ነዉ፡፡የሰበር ችሎቱ ስልጣንም የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞ ሲገኝ ይህንኑ በማረም ላይ የተገደበ መሆኑን ከሰበር ስርዓት መሰረታዊ ዓላማ የምንገነዘበዉ ጉዳይ ነዉ፡፡የኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80/3/ሀ ይዘትና መንፈስ ይህንኑ የሚያመለከት ሲሆን የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 በሰበር ሊታረም የሚገባ መሰረታዊ የህግ ስህተት የሚያሰኙት ሁኔታዎች ምንድናቸዉ ለሚለዉ ትርጉም መሰጠቱ (አንቀጽ 2/4/ ይመለከታል) ሰበር ሰሚ ችሎት የተቋቋመበትን ዓላማ ማለትም ወጥ የህግ አተረጓጎም እንዲኖር እና የዉሳኔዎችን ተገማችነት በማረጋገጥ ረገድ አገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰራ የሚያስችል ነዉ ተብሎ ይታሰባል፡፡

በተለይም በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታዉን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረዉ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ የህገ መንግስቱን ድንጋጌዎች፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ዉሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለዉን ህግ በመጥቀስ ወይም ህግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሆኖ ጉዳዩም አገራዊ ፋይዳን የሚመለከት ሲሆን ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10 (1/ሐ/ እና /መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ከዚህም የምንረዳዉ የሰበር አቤቱታ

የቀረበበት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ ከእነዚህ ሦስቱ ሁኔታዎች ዉጪ ባሉት ሁኔታዎች፣ መሠረታዊ የህግ ስህተትን መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2(4) ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ዉስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለዉ መሆኑን ነዉ፡፡ስለሆነም ይህ የፌዴራል ጠቅላይ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ዉሳኔዉ/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ እነዚህኑ ልዩ ሁኔታዎች ማለትም በአዋጁ አንቀጽ 10(1/ሐ) ላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ከግምት ዉስጥ የማስገባት ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

በተያዘዉ ጉዳይ በሰበር ችሎት ደረጃ እያከራከረ ያለዉ ጉዳይ ሰራተኞቹ ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት አሰሪዉ ወደ ገንዘብ ለዉጦ ለመክፍል  አይገደደም መባሉ ላይ ነዉ፡፡በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ እንደተመለከተዉ የዓመት ፈቃድ ማግኘት የሰራተኛዉ መብት ሲሆን ለአሰሪዉ ግዴታ ነዉ፡፡የዓመት ፈቃድ የሚሰጥበት ጊዜ የሰርተኛዉን ፍላጎት እና አሰሪዉን የሥራ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በሚወጣ  ፈቃድ መስጫ ፕሮግራም መሰረት የሚከናወን መሆኑም ተመልክቷል፡፡በሌላ በኩል በህጉ በግልጽ ካልተፈቀደ በስተቀር የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ መለወጥ አይቻልም፡፡የአመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ ተለዉጦ ለሰራተኛዉ እንዲከፈል የሚደረገዉ የስራ ዉሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የዓመት እረፍት መኖሩ ሲረጋገጥ ነዉ፡፡አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 76--78 ይመለከታል፡፡ከዚህ ሁሉ የምንገነዘበዉ ሰራተኛዉ በህግ የተፈቀደለትን የዓመት እረፍት ተጠቅሞ በአካልም ሆነ በአእምሮ ጤናማ እና ምርታማ ሆኖ ለረጅም ጊዜ እንዲሰራ ለማስቻል መሆኑን ነዉ፡፡በዚህ ጉዳይ የአመልካቾች ጥያቄ ከግንቦት 2011 ዓ.ም እስከ ህዳር 2013 ዓ.ም ያለው የአንድ ሰው 45 ቀናት በቀን ደመወዝ ተለዉጦ ይከፈለን የሚል ነዉ፡፡የጠቀሱትም ምክንያት የስራቸዉ ባህርይ ሹፍርና በመሆኑ ምክንያት ለሾፌር ፈቃድ አይሰጥም ተብለናል የሚል ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ በስራቸዉ ባሕርይ ምክንያት አልተከለከሉም በማለት ፍሬነገሩን ክዷል፡፡የስር ፍርድ ቤትም ይህንን የሚያስረዳ ማስረጃ መቅረቡን አላረጋገጠም፡፡አሰሪዉን ፈቃድ ጠይቀዉ መከልከላቸዉ ተረጋግጧል ቢባል አንኳን ፈቃድ እንዲሰጣቸዉ ከሚገደድ በስተቀር ወደ ገንዘብ ለዉጦ እንዲከፍል የሚያስገድድ አይደለም፡፡ከዚህ አኳያ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ዉሳኔ የሚነቀፍበት ምክንያት አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለል ከላይ እንደተመለከትነዉ የዓመት ፈቃድ ወደ ገንዘብ የሚለወጠዉ በህጉ ሲፈቀድ ብቻ ነዉ፡፡አሰሪዉ የኣመት ፈቃድ ከህግ አግባብ ዉጪ የከለከላቸዉ እንደሆነ መብታቸዉን በህግ አግባብ ማስከበር እንጂ የሥራ ዉል መቋረጡ ሳይረጋገጥ በስራ ላይ ያለ ሰራተኛ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍል አሰሪዉ የሚገደድበት ሁኔታ የለም፡፡ስለሆነም ከአሰሪዉ ጋር ያላቸዉ የስራ ዉል ስለመቋረጡም ሆነ የኣመት ፈቃድ ጠይቀዉ ስለመከልከላቸዉ አለማስረዳታቸዉን በማረጋገጥ የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ ለዉጦ ለመክፍል ተጠሪ አይገደድም በማለት የክልሉ ሰበር ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ የአሰሪና ሰራተኛ ሀጉንና የቀረበዉን ክርክር ይዘት ያገናዘበ ነዉ ከሚባል በስተቀር በፌደራል ፍርድ ቤቶች በአዋጅ ቁ/1234/2013 አንቀጽ 10 (1/ሐ/ ስር ከተመለከቱት ድንጋጌዎች አንፃር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አልተገኘም፡፡ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

**<u>ዉሳኔ</u>**

1ኛ/የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መ/ቁጥር 376004 ላይ በቀን 29/10/2013 ዓ.ም በዋለዉ ችሎት የሰጠዉ ዉሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥርዓት ህግ ቁ/ 348(1) መሠረት ጸንቷል፡፡

2ኛ/በዚህ ችሎት የተደረገ ክርክር ያስከተለዉን ወጪ እና ኪሳራ ግራ ቀኝ የየራሳቸዉን ይቻሉ፡፡
**መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ**

አ/መ የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት